14.09.1998

# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት አስተባባሪ ኮሚቴ የመጀመሪያ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ

የስብሰባ ቦታ ፓሪስ
የስብሰባው ተካፋዮች -- ስምንቱም የህብረቱ ቋሚ ተወካዮች ተገኝተዋል::

| የስብሰባው ተካፋይ ድርጅቶች | የተወካይ ስም |
|---|---|
| 1. ከኢዴኃቅ | 1. ዶ/ር ነገደ ጎበዜ (በአስተ.ኮ ቋሚ ተወካይ ስለአልተመደበ ሁለቱም ተገኝተዋል::) 2. አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ |
| 2. ከአማራጭ ኃይሎች | ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ |
| 3. ከደቡብ ኅብረት | አቶ ኢያሱ ወ/ጻድቅ |
| 4. ከመድኅን | አቶ ማሞ ይሁኔ |
| 5. ከትዲት | አቶ አረጋዊ በርኼ |
| 6. ከአብኮ | አቶ ገዛኸኝ ኃይሉ |
| 7.ከትትኢ-ኢቡሶ. | አቶ አሰፋ ሀብቱ |
| 8.ከአርዱፍ | አልተገኘም |

የአስተባባሪ ኮሚቴው ስብሰባውን ዶ/ር ነገደ ጎበዜን በሊቀመንበርነት አቶ ማሞ ይሁኔን በጸሐፊነት በመሰየም ስብሰባውን ጀመረ::

የስብሰባው የመነጋገሪያ ርዕሶች

1ኛ/ የህብረቱን ልዩ ልዩ ሰነዶችን በሚመለከት
2ኛ/ ስለ ህበረቱ አስተባባሪ ኮሚቴና ጽ/ቤት መመሥረት
3ኛ/ ስለ ህበረቱ ድርጅታዊ መዋቅር በመድኅን በቀረበው ሰነድ ላይ በመመሥረት መነጋገር የሚሉትን ናቸው::

## 1ኛ/ የሶስቱን ቀናት ጉባዔ ማጠቃለያ ሰነዶችን በሚመለከት

በዚሁ ርዕስ አጠር ያለ የሀሳብ ልውውጥ ተደርጎ ጉባዔው ያጸደቃቸው ሰነዶችና ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው ለዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ እንዲያግዙ ለማድረግ የሚከተለው የትርጉም የሥራ ክፍፍል ተደርጓል::

1.1. የዴሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም የሚለውን ዶ/ር በየነና ረ/ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ወደ እንግሊዝኛ እንዲተረጉሙ

1.2. ጉባዔው ያደረገውን ግንዛቤና ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ዶ/ር በየነና ረ/ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና እንዲተረጉሙት ተወስኗል::

1.3. ከሁለተኛው የፓሪስ ጉባዔ የቀረበውን የብሔራዊ ውይይት ጥሪን በሚመለከት አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ወደ እንግሊዝኛ እንዲተረጉሙት ሀሳብ ቀርቦ እርሳቸውም ተቀብለውታል:: በአማርኛ የተዘጋጁት ሰነዶች ተስተካክለውና ተሟልተው እንዲጻፍ ተጨማሪ ሀሳብ ቀርቦ አቶ ማሞ ይሁኔ ሦስቱንም ሰነዶች አጠናቀው ለማቅረብ ተስማምተው የመጀመሪያው የመወያያ ርዕስ አብቅቷል::

## 2ኛ/ ስለ ህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴና ጽ/ቤት መመሥረት

የኢተፖድኅን አስተባባሪ ኮሚቴንና ጽ/ቤት በሚመለከት ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል:: በዚህ የመነጋገሪያ ርዕስ ስር የአስተባባሪ ኮሚቴው ተጠናክሮ መቀጠል መሠረት ለተጣለለት የህብረት ትግል ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን የኅብረቱ ማዕከል የት መሆን እንዳለበት ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል::

1ኛ/ አገር ቤት መሆን አለበት የሚለው ሀሳብ ቀርቦ አስተባባሪው ኮሚቴ በሰፊው ተነጋግሮበታል::ሀሳቡን ያቀረበው ክፍል የአስተባባሪው አካልና ጽ/ቤት አገር ውስጥ መሆን ትግሉን የበለጠ ሊያግዝ የሚችል መሆኑን በመግለጽ ያቀረበ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይኼንን ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ባለመቀበል:-

2ኛ/ የአስተባባሪው ኮሚቴና የኅብረቱ ማዕከል በውጭ አገር መሆን አለበት የሚለው ሀሳብ ቀርቧል::ለዚህም በበርከታ የህብረቱ አባል ድርጅቶች ተወካዮች ሰፋ ያለ ማብራሪያ የቀረበ ሲሆን ጠቅለል ባለመልኩ ከተነሱት ውስጥ
ሀ/ የህበረቱ በርካታ አባል ድርጅቶች በውጭ አገር መገኘት
ለ/ አሁን ለተፈጠረው ኅብረትና ለተወሰዱት አቋሞች በሥልጣን ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ መንግሥት አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል ሳይታወቅ በአገር ውስጥ ማዕከሉን መመሥረት አደገኛ ነው የሚል ሲሆን÷
ሐ/ኅብረቱ ገና ሳይፈጠር እንዳይቀጭ ያለውን ሥጋት ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊነትን በመቀበልና በውጭ ያለውን ኃይል የበለጠ በማስተባበር በቂ የድጋፍ መሠረት በመጣልና የተባበረና የተቀነባበረ ዲፕሎማሲያዊ የድጋፍ ማሰባሰብ ጥረት ከተደረገ በኋላና
መ/ ኅብረቱ ተጠናክሮ አንድ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲደርስ በአገሪቱ ውስጥ ሊፈጠር በሚችል አመቺ ሁኔታ ቀስ በቀስ ወደ አገር ቤት እንዲገባ ማድረጉ ተገቢነት ያለው መሆኑን በመግለጽ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ የህብረቱ ማዕከል አውሮፓ እንዲሆን በሙሉ ድምፅ ተወስኗል::
ከዚህም በማያያዝ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴና ጊዜያዊ ጽ/ቤት የሚለውም ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ በተሰብሳቢው ተቀባይነት አላገኘም:: በዚሁም ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ቋሚ አስተባባሪው ኮሚቴ ማዕከሉን በአውሮፓ በማድረግ

1ኛ/ በአሜሪካና
2ኛ/ በኢትዮጵያ በኅብረቱ አባል ድርጅቶች ቅርንጫፎችን እንዲያቋቁም፤
3ኛ/ አስተባባሪው ኮሚቴ የዕለት ተዕለት የኅብረቱን የሥራ ክንውኖች ለማከናወን የሚያስችለው አንድ ከአስተባባሪው ኮሚቴ ውስጥ አራት አባላት የሚገኙበት ቋሚ ሰክሬታሪያት እንዲኖረውና የአውሮፓን አህጉር የሚያስተባብር ደግሞ አንድ አስተባባሪ በሰክሬታሪያቱ እንዲመደብ ተወስኗል::
በዚሁም መሠረት ለአስተባባሪው ኮሚቴ ቋሚ ሰክሬታሪያት ተመርጧል::
1ኛ/ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ (ኢዴኃቅ ቋሚ ተወካይ ባለመወከሉ ) በጊዜያዊ ሰብሳቢነት
2ኛ/ አቶ አረጋዊ በርኼ በምክትል ሰብሳቢነት
3ኛ/ አቶ ማሞ ይሁኔ በዋና ጸሐፊነት
4ኛ/ አቶ ኢያሱ ወልደጻዲቅ በገንዘብ ያዥነት
እንዲያገለግሉ የአስተባባሪ ኮሚቴው ወስኗል::

## 3ኛ/ የህብረቱን ድርጅታዊ መዋቅር በሚመለከት

ሦስተኛውና የመጨረሻው የአስተባባሪው ኮሚቴ የመነጋገሪያ ርዕስ ቀደም ብሎ በተካሄደው ጉባዔ ላይ በኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) የሚፈጠረውን የኅብረት ድርጅታዊ መዋቅር ሰነድ የሚሻሻለው ተሻሽሎ የሚጨመረው ተጨምሮና የሚወሰደው እንዳለ ተወስዶ ሥራ ላይ እንዲውል

በጉባዔው የተወሰነውን ተግባራዊ ለማድረግ በኅብረቱ ድርጅታዊ መዋቅር ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል። በዚሁም መሠረት፡-

1ኛ/ ለህብረቱ ሰነድ መግቢያነት፥ ዓላማና ተግባር ከጉባዔው የዴሞክራሲ ሂደትና ትልም ከሚለው መግቢያ እንዲወሰድ፤

2ኛ/ከመድኅን ከቀረበው ሰነድ አንዳንድ አንቀጾችና ንዑስ አንቀጾች እንዲሻሻሉና እንዲለወጡ በማድረግ አ/ኮሚቴው አጽድቋቸዋል።
እንዲሻሻሉ የተደረጉ አንቀጾች

3፥4፥7፥18፥19

እንዳለ የተወሰዱ
5፥ 6፥ 8፥9፥10፥11፥12፥13፥

በመድኅን ከቀረበው ሰነድ ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ ወይም ይዘታቸው በሌሎች አንቀጾች እንዲካተቱ የተደረጉ፤
መግቢያ፥2፥14፥15፥16፥17፥20 ናቸው።

<u>በማጠቃለያም</u>

የአስተባባሪው ኮሚቴ ሌሎችንም በማሳሰቢያነት በቀረቡ ጉዳዮች፥ ህብረቱን ለማጠናከር መወሰድ በሚገባቸው የዲፕሎማሲ፥ ድርጅታዊና አጠቃላይ የፕሮፓጋንዳ ስራዎች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ተስማምቷል።
የህብረቱን ድርጅታዊ መዋቅር አስመልክተው የተሻሻሉ አንቀጾች ታርመውና ተስተካክለው ሥራ ላይ እንዲውሉ ጥረት እንዲደረግ ተወስኗል።

| <u>የጉባዔው ሰብሳቢ</u> | <u>የጉባዔው ቃለ ጉባዔ ጸሐፊ</u> |
|---|---|
| ዶ/ር ነገደ ጎበዜ | ማሞ ይሁኔ |